# የእነሱስ ተመለሰ የእኛስ?!!!

**በሕገወጥ መንገድ የተወሰደ ንብረት ለሕጋዊ ባለቤት መመለሱ አያከራክርም:: ሆኖም የመለስ አገዛዝ ለመለስ እናት ሀገር ተወላጆች ይህን ያህል ሲጨነቅ፣ ከኤርትራ ሲባረሩ ንብረታቸውን ስለተቀሙትስ ኢትዮጵያዊን ምነዋ ዝምታን መረጠ?**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ኤምባሲ
ፓ ሪ ስ

Embassy of the Federal Democratic
Republic of Ethiopia
Paris

Date 08-12-2001

N° ኢ-ኤ-ፓ/01-153/84/01

**ለኤርትራውያንና ትውልድ ኤርትራውያን በሙሉ**

ግንቦት 7 ቀን 2001 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ባወጣው መመሪያ መሰረት በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ንብረታቸውን ሳይሸጡ(ገንዘባቸውን ሳይወስዱ) ኢትዮጵያ ውስጥ ትተው የሄዱትን ኤርትራውያንን ንብረት በተመለከተ አስፈላጊውን ማጣራት ተደርጎ ንብረታቸውን እንዲመለስላቸው ማድረግ እንዲቻል የቅድሚያ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል ::

በዚሁም መሰረት ንብረቱን የሚያስመልስ ኮሚቴ በጦርነቱ ወቅት ንብረታቸውን ሳይሸጡ ትተው የወጡ ኤርትራውያን ባለንብረቶች(ባለቤቶች) የሚሞሉት ፎርም አዘጋጅቷል ::

ስለሆነም ንብረቶቻችሁን ሳትሸጡ (ገንዘባቹህን ሳትወስዱ) ከኢትዮጵያ የወጣችሁ ኤርትራውያን (በትውልድ ኤርትራውያን) በሙሉ ኢትዮጵያ ኤምባሲ ድረስ በመምጣት ፎርሙን እንድትሞሉ እናሳስባለን ::

ከሰላምታ ጋር

አምባሲው

አድራሻ :- 35 Avenue Charles Floquet 75007 Paris

ፎርም መሙያ ሰዓት :- ከሰኞ- አርብ 9hr-13hr, 14hr-17hr

35, Avenue Charles Floquet - 75007 Paris - Tél 01 47 83 83 95 - Télécopie 01 43 06 52 14